Made with Xodo PDF Reader and Editor

Daniel Fikadu Law Office

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN MEDIA AUTHORITY

# የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 መሻሻያ ረቂቅ አዋጅ

የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ

Made with Xodo PDF Reader and Editor



**አዋጅ ቁጥር………/2017**

**<u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መገናኛ ብዙሃን (ማሻሻያ) አዋጅ</u>**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መገናኛ ብዙሀን አዋጅ ፀድቆ በስራ ላይ የዋለ ቢሆንም አዋጁ ተግባራዊ ሲደረግ ከመገናኛ ብዙሃን ሪጉላቶሪ ሥልጣንና ተግባራት አንጻር አስተዳደራዊ ክፍተቶች የተስተዋሉ በመሆኑ፣

እነዚህን ክፍተቶች በማስተካከል የመገናኛ ብዙኃን ዘርፉን በአግባቡ ለማስተዳደር እንዲቻል የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013ን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራሊዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1.**<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ **"የመገናኛ ብዙሃን (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር……/2017"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2.**<u>ማሻሻያ</u>**

የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፤

1/ የአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ተሰርዘዋል፡፡ ከንዑስ አንቀጽ 4 ጀምሮ ያሉት ንዑስ አንቀፆች እያንዳንዳቸው እንደቅደም ተከተላቸው ወደ ንዑስ አንቀጽ 2 እና ተከታዮቹ ተሸጋሽገዋል፤ ፡

2/ የአዋጁ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 5(ሀ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (5)(ሀ) ተተክቷል፤

(5)(ሀ) የቦርዱ አባላት ለመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ቅርበትና አግባብነት ካላቸው የተለያዩ አካላት እና የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ይሆናሉ፤

3/ የአዋጁ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 6 ተሰርዟል፡፡ ንዑስ አንቀጽ 7 ወደ ንዑስ አንቀጽ 6 ተሸጋሽጓል፤

Made with Xodo PDF Reader and Editor



4/ የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 4 ተሰርዟል፡፡ ከነባሩ ንዑስ አንቀጽ 5 ጀምሮ ያሉት ንዑስ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ወደ ንዑስ አንቀጽ 4 እና ተከታዮቹ ተሸጋሽገዋል፤

5/ የአዋጁ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ተተክቷል፤

(2) በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው ውክልና፤ መመሪያ ማውጣትን፣ ይግባኝ መመልከትን እና ቦርዱ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 12 ንዑስ አንቀፅ (2) እና (3) የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር አያካትትም፤

6/ የአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ 1 ተተክቷል፤ እንዲሁም በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 5 ላይ (3) በሚል የተገለፀው የማጣቀሻ ቁጥር (4) በሚል እንዲስተካከል ተደርጓል፡፡

(1) የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማል፡፡

7/ የአዋጁ አንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ (1) በሚከተለው መልኩ ተስተካክሏል፤

(1) ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፈቃድ ክፍያ፣ እና ዓመታዊ የፈቃድ ማሳደሻ ክፍያ ለኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን መክፈል ይኖርበታል፡፡ ለተመደበለት የሬዲዮ ሞገድ ዓመታዊ የሬዲዮ ሞገድ ክፍያን ለኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን መክፈል ይኖርበታል፡፡

8/ የአዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) ተተክቷል፤

(1)(ረ) የማናቸውም ፕሮግራም ይዘት በጣቢያው ከመሠራጨቱ በፊት ወይም በሚሰራጭበት ጊዜ ሕግን የሚያከብር መሆኑን የማረጋገጥ፤

9/ የአዋጁ አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ (1) የእንግሊዝኛው ትርጓሜ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (1) ተተክቷል፡፡

Made with Xodo PDF Reader and Editor

Daniel Fikadu Law Office

(1) The Authority may step by step take, as may be appropriate, the following administrative measures, where a media service provider contravenes the provisions of this Proclamation and Regulations or Directives issued in accordance with this Proclamation:

10/ የአዋጁ አንቀጽ 81 ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ 3 እና 4 ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1፣ 2፣ እና 3 ተተክተዋል፤ ንዑስ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 ሆኖ ተሸጋሽጓል፡፡

(1) የፈቃድ ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀት አለማደስ፣ ማገድ፣ መሰረዝ፣ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ ከባድ የገንዘብ ቅጣት ወይም አንድ ፕሮግራም ማገድ ወይም መሰረዝ የሚያስከትሉ ውሳኔዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ይሆናል፤

(2) ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ውስጥ የፈቃድ ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀት አለማደስ፣ መሰረዝ፣ ከባድ የገንዘብ ቅጣት ወይም አንድ ፕሮግራም መሰረዝ የሚያስከትል ቅጣት የሚጻርግ ክስ ሲቀርብለት ባለፈቃዱ ወይም የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መገናኛ ብዙሃን በጉዳዩ ላይ ያለውን ምላሽ በፅሁፍ በ7 የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጠው ይገባል፤

(3) በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (1) መሠረት በተወሰኑት ውሳኔዎች ቅር የተሰኘ ባለፈቃድ ወይም የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠው የመገናኛ ብዙሃን ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፤ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

11/ የአዋጁ አንቀጽ 82 ንዑስ አንቀጽ 1 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል፡፡

(1) በዚህ የማሻሻያ አዋጅ አንቀጽ 2 ንኡስ አንቀጽ10(3) መሰረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ወገን ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

Made with Xodo PDF Reader and Editor

3 **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ……………..ቀን 2017 ዓ.ም

**ታዬ አፅቀስላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

Daniel Fikadu Law Office